# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

## ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ



| ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | |
|---|---|
| ግዛት | ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ እስከ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. |
| በዓለ ንግሥ | ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. |
| ቀዳሚ | ንግሥት ዘውዲቱ |
| ተከታይ | ዓፄ አምሃ ሥላሴ (በስደት) |
| ባለቤት | እቴጌ መነን |
| ልጆች | ልዕልት ሮማንወርቅ<br>ልዕልት ተናኘወርቅ<br>ዓፄ አምሀ ሥላሴ<br>ልዕልት ዘነበወርቅ<br>ልዕልት ፀሀይ<br>ልዑል መኮንን<br>ልዑል ሣህለ ሥላሴ |
| ሙሉ ስም | ራስ ተፈሪ መኮንን |
| ሥርወ-መንግሥት | ሰሎሞን |
| አባት | ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ጉዴሳ |
| እናት | ወ/ሮ የሺመቤት አሊ |
| የተወለዱት | ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፰፻፹፬ ዓ.ም. |
| የሞቱት | ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. |
| ሀይማኖት | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና |

**ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ (ቀ.ኃ.ሥ.)** ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ እስከ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ።

ተፈሪ መኰንን ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፬ ዓ.ም. ከአባታቸው ከልዑል ራስ መኰንን እና ከእናታቸው ከወይዘሮ የሺ እመቤት ኤጀርሳ ጎሮ በተባለ የገጠር ቀበሌ ሐረርጌ ውስጥ ተወለዱ።

በ፲፰፻፺፱ የሲዳሞ አውራጃ አገረ ገዥ ሆኑ። በ፲፱፻፫ ዓ.ም. የሐረርጌ አገረ ገዥ ሆኑ። የሐረርጌ አገረ ገዥ ሲሆኑ፣ በጣም ብዙ ሺህ ተከታዮች ነበሩዋቸውና ልጅ እያሱን ከእንደራሴነት በኀይል እንዳያስወጡ፤ እያሱም ተፈሪን ከሐረር አገረ ገዥነት እንዳይሽሯቸው የሚል ስምምነት ተዋዋሉ። ዳሩ ግን እያሱ ሃይማኖታቸውን ከክርስትና ወደ እስልምና እንደቀየሩ የሚል ማስረጃ ቀረበና ብዙ መኳንንትና ቀሳውስት ስለዚህ ኢያሱን አልወደዱዋቸውም ነበር፣ ከዚህም በላይ እያሱ ተፈሪን ከሐረር ከአገረ ገዥነታቸው ለመሻር በሞከሩበት ወቅት ስምምነታቸው እንግዲህ ተሠርዞ ተፈሪ ደግሞ ለወገናቸው ከስምምነቱ ተለቅቀው በዚያን ጊዜ እሳቸው እያሱን ከእንደራሴነት አስወጡ። እንግዲህ በ፲፱፻፱ ዓ.ም. መኳንንቱ ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥት ሆነው አድርገዋቸው ተፈሪ ደግሞ እንደራሴ ሆኑ። ከዚህ ወቅት ጀምሮ ተፈሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለሙሉ ሥልጣን ነበሩ። በመስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. የንጉሥነት ማዕረግ ተጨመረላቸው። በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ንግሥት ዘውዲቱ አርፈው ንጉሠ ነገሥት ሆኑና ጥቅምት ፳፫ ቀን፲፱፻፳፫ ዓ.ም.፣ ብዙ የውጭ ልዑካን በተገኙበት ታላቅ ሥነ ሥርዓት ቅብዓ ቅዱስ ተቀብተው እሳቸውና ሚስታቸው እቴጌ መነን ዘውድ ጫኑ።



ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ፤ ንጉሠ ነገሥት ፲፱፻፳፫ - ፲፱፻፷፯

በንግሥ በዓሉ ዋዜማ፤ ጥቅምት ፳፪ ቀን የትልቁ ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ ዓጼ ሚልክ ሐውልት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ፤ ለዘውድ በዓል የመጡት እንግዶች በተገኙበት ሥርዐት፣ የሐውልቱን መጋረጃ የመግለጥ ክብር ለብሪታንያ ንጉሥ ወኪል ለ(ዱክ ኦፍ ግሎስተር) ተሰጥቶ ሐውልቱ ተመረቀ።

ለንግሥ ስርዐቱ ጥሪ የተደረገላቸው የውጭ አገር ልኡካን ከየአገራቸው ጋዜጠኞች ጋር ከጥቅምት ፳ ቀን ጀምሮ በየተራ ወደ አዲስ አበባ ገብተው ስለነበር ሥርዓቱ በዓለም ዜና ማሰራጫ በየአገሩ ታይቶ ነበር። በተለይም በብሪታንያ ቅኝ ግዛት በጃማይካ አንዳንድ ድሀ ጥቁር ሕዝቦች ስለ ማዕረጋቸው ተረድተው የተመለሰ መሢህ ነው ብለው ይሰብኩ ጀመር። እንደዚህ የሚሉት ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ፊተኛው ስማቸው «ራስ ተፈሪ» ትዝታ ራሳቸውን «ራስታፋራይ» (ራስተፈሪያውያን) ብለዋል።

ዓጼ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ እንደጫኑ የአገሪቱን የመጀመሪያ ሕገ መንግሥት እንዲዘጋጅ አዝዘው በዘውዱ አንደኛ ዓመት በዓል ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ.ም. በአዲሱ ምክር ቤት (ፓርላማ) ለሕዝብ ቀረበ። ከዚህም በላይ ብዙ የቴክኖዎሎጂ ስራዎችና መሻሻያዎች ወደ ኢትዮጵያ ከውጭ አገር አስገቡ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የሙሶሊኒ ፋሺስት ሠራዊት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ጃንሆይ በቆራጥነት ከታገሉ በኋላ የጠላቱ ጦር ኀይል ግን በመጨረሻ ወደ እንግሊዝ አገር ለጊዜው አሰደዳቸው። ወደ ጄኔቭ ስዊስ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ሄደው ስለ ጣልያኖች የዓለምን እርዳታ በመጠየቅ ተናገሩ። የዓለም መንግሥታት ግን ብዙ አላደረጉም። በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. ግን አውሮፓ ሁሉ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተያዘ። የእንግሊዝ ሠራዊቶች ለኢትዮጵያ አርበኞች እርዳታ በመስጠት ጣልያኖች ተሸንፈው በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ኢትዮጵያን ተዉ። ዓፄ ኃይለ ሥላሴ አዲስ አበባን እንደገና የገቡበት ቀን ከወጡበት ቀን በልኩ ዕለት አምስት ዓመት በኋላ ነበረ።




ልጅ ተፈሪ መኮንን በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም.

በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም. ግርማዊነታቸው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ እንዲመሠረት ብዙ ድጋፍ ሰጡ። በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ወደ ካሪቢያን ጉብኝት አድርገው የጃማይካ ራስታዎች ተገኛኙ። በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. በማርክሲስት አብዮት ደርግ ሥልጣን ያዙና እሳቸው በእሥር ቤት ታሰሩ። በሚከተለው ዓመት ከተፈጥሮ ጠንቅ እንደ አረፉ አሉ፤ ሆኖም ለምን እንደ ሞቱ ስለሚለው ጥያቄ ትንሽ ክርክር አለ። ብዙ ራስታዎች ደግሞ አሁን እንደሚኖሩ ይላሉ።

# የህይወት ታሪክ

የዓፄ ኃይለ ሥላሴ የትውልድ ስም **ልጅ ተፈሪ መኮንን** ነው። ስመ መንግሥታቸው **ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ** ነበር። **ሞዓ አንበሣ ዘእምነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ** የሚለው የሰሎሞናዊ ሥረወ-መንግሥት ነገሥታት መጠሪያም በንጉሠ ነገሥቱ አርማ እና ሌሎች ይፋዊ ጽሑፎች ላይ ከመደበኛው ማዕረግ ጋር ይጠቀስ ነበር። **ጃንሆይ**፣ **ታላቁ መሪ** እና **አባ ጠቅል** በመባልም ይታወቁ ነበር።

## ጥቅስ

«አንዳንድ ሰዎች የሕይወቴን ታሪክ ጽፈው ባለማወቅ ወይም በመሳሳት ወይም በምቀኝነት ዕውነትን አስመስለው ለሌሎች እንዲመስል ቢሞክሩም የዕውነተኛውን ነገር ከሥፍራው ሊያናውጡት አይችሉም።»

— *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ* (*መቅደም*)

| | |
|---|---|
| ዛግዌ ሥርወ-መንግሥት | ቅዱስ ሐርቤ · ገብረ መስቀል ላሊበላ · ዓፄ ነዓኵቶ ለአብ |
| ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት | ዓፄ ይኩኖ አምላክ · ይግባ ጽዮን · ሰይፈ አርድ ፬ኛ · ህዝብ አስገድ · ቅድመ አስግድ · ጅን አሰገድ · ሳባ አሰገድ · ወደም አራድ · ዓፄ ዐምደ ጽዮን · ንዋየ ክርስቶስ · ዓፄ ንዋየ ማርያም · ቀዳማዊ ዓፄ ዳዊት · ቀዳማዊ ዓፄ ቴዎድሮስ · ዓፄ ይስሐቅ · ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ · ዓፄ በእደ ማርያም · ዓፄ እስክንድር · ዓፄ አምደ ጽዮን ፪ኛ · ዓፄ ናዖስ · ዓፄ ልብነ ድንግል · ዓፄ ገላውዴዎስ · ዓፄ ሚናስ · ዓፄ ሠርፀ ድንግል · ዓፄ ያዕቆብ · ዓፄ ዘድንግል · ዓፄ ሱስንዮስ · ዓፄ ፋሲል · ቀዳማዊ ዓፄ ዮሐንስ · ቀዳማዊ ዓፄ ኢያሱ · ዓፄ ተክለ ሃይማኖት · ዓፄ ቴዎፍሎስ · ዓፄ ዮስጦስ · ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት · ዓፄ በካፋ · ዳግማዊ ዓፄ ኢያሱ · ዓፄ ኢዮዋስ |
| ዘመነ መሳፍንት | ራስ ዓሊ (ትልቁ) · ራስ ዓሊጋዝ · ራስ ዐሥራትና ራስ ወልደ ገብርኤል · ራስ ጉግሣ · ራስ ይማም · ራስ ማርዬ · ራስ ዶሪ · ራስ ዓሊ (ትንሹ) |
| ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት | ዓፄ ቴዎድሮስ · ዓፄ ዮሐንስ ፬ኛ · ዳግማዊ ዓጼ ምኒልክ · ልጅ ኢያሱ · ንግሥት ዘውዲቱ · **ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ** |

**ምንጭ** ፡ ውክፔዲያ (Wikipedia.org)